# ሀገር አቀፍ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ

ትምህርት ሚኒስቴር

መጋቢት 2007 ዓ.ም

# 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲን በመቅረፅና ልዩ ልዩ የአተገባበር ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ቀድሞ በትምህርት ዘርፍ ይታዩ የነበሩትን የተደራሽነት፣ የፍትሀዊነት፣ የአግባብነትናየጥራት ችግሮችን በመፍታት በኩል ሰፊና ውጤታማ ስራዎችን በመስራት የነበሩትን ችግሮች በመፍታት በኩል አበረታች ውጤትመመዝገቡ ይታወቃል። በመሆኑም ሁሉም ህጻናት በመማር ማስተማሩ ሂደት ተፈላጊውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት አዳብረው በሀገሪቷ ሁለንተናዊ ዕድገት ዋነኛ ተዋናይ እንዲሆኑ ለማድረግ የትምህርት ጥራቱን ማረጋገጥ አንዱና ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን በመገንዘብ በ 1999 ዓ.ም.የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅተቀርፆ በመተግበር ላይ ይገኛል።

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በውስጡ 6 መርሃ ግብሮችን አካቶ ይዟል። እነሱምየመምህራን ልማትመርሃ ግብር፤ የትምህርት ቤት መሻሻልመርሃ ግብር፣የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት መርሃ ግብር፣የአጠቃላይ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ማሻሻያ መርሃ ግብር፤ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት የማስፋፋት መርሃ ግብር እናየአጠቃላይ ትምህርት አመራር፣አሰራርና አደረጃጀት ማሻሻያ መርሃ ግብርናቸው።

በአጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ላይ እንደተገለጸው የቅድመ-መደበኛ ትምህርት የትምህርት ጥራትን በማሳደግና መጠነ-ማቋረጥን በመቀነስ፣ ፍትሀዊነትን በማስፈንና የህጻናት የመማር መብትን በማረጋገጥ በኩል ቅድሚያ ከሚሰጣቸው የትምህርት ዕርከኖች መካከልአንዱ ነው።

በዚህም መሰረት በሀገር አቀፍ ደረጃ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት አግባብነትን ፣ ፍትሀዊነትና ጥራትን እንዲሁም የህጻናትን ተፈጥሯዊ የመማር ሁኔታን ባገናዘበና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን እንዲቻል ይህሀገር አቀፍየቅድመመደበኛ ትምህርት ኢንስፔክሽንማዕቀፍተዘጋጅቷል።

# 2. የቅድመመደበኛ ትምህርት ኢንስፔክሽን አላማዎች

## 2.1. አጠቃላይ አላማ

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዋና ዓላማ የትምህርት ተደራሽነትን፣ፍትሃዊነትን፣አግባብነትና ጥራትንበማረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ የህፃናትን የአካል፣ የአዕምሮ፣ የስሜትና የማህበራዊ ግንኙነትን በማሳደግ ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው ።

## 2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- የቅድመመደበኛ ትምህርት ወጥ በሆነ መልኩ ተደራሽነትን በማሻሻል፣ፍትሀዊነትንና ተገቢነትን በጠበቀ መልኩ እንዲሰጥ ለማስቻል፣
- የቅድመመደበኛ ትምህርት ቤቶች ለህጻናት ምቹና ለደህንነታቸው የማያሰጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ህፃናት ከአካባቢያቸውናእርስ በርሳቸው  በቀላሉ የሚግባቡባቸው ተቋማት እንዲሆኑ ለማስቻል፣
- የትምህርቱ አቀራረብ በዋናነት በጨዋታና በአሳታፊነት ላይ ያተኮረ ሆኖ ህጻናትን እያዝናና የሚያስተምር እንዲሆን ለማስቻል፣

- የቅድመመደበኛ ትምህርት ቤቶች ህጻናት ችሎታቸውን የሚለዩባቸው፣የሚያዳብሩባቸውና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህጻናት እንደፍላጎታቸው ትምህርት የሚያገኙባቸው ማዕከላት መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣
- በቅድመ-መደበኛ ትምህርት የወላጆችና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጠናከር አቀራረቡ በተግባቦትና በመስተጋብር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- መምህራን፣ረዳት መምህራንና ሞግዚቶች ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ፣
- የመረጃ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ በስታንዳርዱመሰረትመሆኑን ለማረጋገጥ

## 3. የቅድመመደበኛ ትምህርት ኢንስፔክሽን መሪመርሆዎች

- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን ስራብሰለጠኑናገለልተኛ ወይም የትምህርት ቤቱ አካል ባልሆኑ የትምህርት ኢንስፔክተሮች ይካሄዳል፣
- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤቶች የአፈጻጸም ግምገማ በመረጃ ላይ ተመስርቶ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ይሆናል፣
- ግምገማው ጠንካራ ጎኖችን የሚያበረታታና በተለዩ እጥረቶች ላይ የማሻሻያ ሀሳብ በመስጠት ለበለጠ ውጤት የሚያነሳሳ ይሆናል፣
- ስታንዳርዱንመሰረት በማድረግ ለውጤታማነት የሚያነሳሳ ግብረመልስ በኢንስፔክሽኑ ለተካተቱ ትምህርት ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፣
- የኢንስፔክሽኑ አካሄድ በተዘጋጀው መስፈርት እንጂ በግለሰባዊ ስሜት ላይ የተመረኮዘ መሆን የለበትም፣
- የኢንስፔክሽን ስራው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በማክበር የሚከናወን ይሆናል።

## 4. የቅድመ መደበኛ ትምህርትኢንስፔክሽን አስፈላጊነት

የሀገራችን አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሚሰጠው ትምህርት ሕፃናትን ለተስተካከለ የአካልና የአእምሮ የስሜትና የማኅበራዊ ግንኙነት እድገትና ለመደበኛ ትምህርት የሚያመቻች እንደሚሆን ያስቀምጣል። የአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ህጻናት ተገቢውን እንክብካቤ የሚያገኙበት፣ አካላቸውንና አእምሯቸውን የሚያዳብሩበት፣ በየደረጃው እንደፍላጎታቸው ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት የትምህርት ዕርከን ነው። በተጨማሪም ህፃናት በቀጣይ ለሚሳተፉባቸው የትምህርት ዕርከኖች መሰረት የሚጥልና የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል፣ መጠነ-ማቋረጥንና መጠነ-መድገምን ለመቀነስ የሚያስችል በመሆኑ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው የትምህርት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ያመለክታል።

በዚህም መሰረት የቅድመመደበኛ ትምህርት ወጥ በሆነ አሰራር ፍትሀዊነትን፣ተደራሽነትን፣ አግባብነትንና ጥራትን ጠብቆ እንዲከናወን ለማስቻል ሁሉም ክልሎችና ትምህርት ቤቶች የሚተገብሩት ሀገርአቀፍ የቅድመመደበኛ ትምህርት ኢንስክሽን ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑታምኖበታል።

## 5. የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነ-ምግባር

- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ በሚያከናውናቸውየኢንስፔክሽንተግባራት ሙያዊ አቀራረብ ሊኖረው ይገባል፣
- ኢንስፔክተሩ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር የሚያደርጋቸው ውይይቶችና ግንኙነቶች በመከባበር ላይ የተመሰረቱ ሊሆን ይገባል፣

- አንድ ኢንስፔክተር በተቻለ መጠን የትምህርት ቤቱን ስራ ሳያስተጓጉል ስራውን ለማከናወን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፤ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያስከፋ ተግባራትንማከናወን የለበትም፣
- በሀገር አቀፉ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍና የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን መመሪያ መሠረት ሥራውን ያከናውናል፣
- ውሳኔዎች ላይ ሲደርስ  በተጨባጭ መረጃ ፣ ሚዛናዊነትና ፍትሃዊነትን በጠበቀ መልኩና ግልፅነት በተሞላበት ሁኔታ መሆን አለበት፣
- ከትምህርት ቤቱ ጋር የሚደረግ ውይይት ት/ቤቱን የሚገነባ፣ ውጤትን ሊያመጣ የሚችል እንጂ ስህተት ፈላጊ መሆን የለበትም። በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱን የወደፊት መሻሻል የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፣
- በኢንስፔክሽን ስራ ወቅት  የተሰበሰበ መረጃን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት።

# 6. የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች /Focus Areas of Inspection

| መለኪያ | የትኩረት መስኮች |
|---|---|
| ግብዓት | የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ   ምንጮች |
| | ምቹየመማሪያአካባቢ |
| | የምድረ ግቢ ገጽታና አደረጃጀት |
| ሂደት | እንክብካቤና -መማር፡- |
| | እንክበካቤ |
| | መማር |
| | የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት |
| | ስርዓተ ትምህርት |
| | ምዘና |
| | የትምህርት ቤት፣ የወላጆችና የማህበረሰብ አጋርነት |
| ውጤት | ትምህርት ቤቱና ህፃናት ያስመዘገቡት ውጤት |
| | የህፃናት ተሳትፎ እና የውስጥ ብቃት |
| | የህፃናት ግለ-ስብዕና |
| | የመምህራንና የትምህርት አመራር ግለ - ስብዕና |
| | የወላጆችና የአካባው ማህበረሰብ ተሳትፎ |

# I. ግብዓት(30%)

**የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች**

ስታንዳርድ **1**

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል (6%) ።

አመልካቾች፡-

I.1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሕንፃዎች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከሲሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ከመሳሰሉት የተሰሩ ናቸው ። (1%)

I.2. ህንፃው የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ነው ። (1%)

I.3. ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ፣ የህፃን-ክፍል ጥምርታ፣የህፃን መምህር ጥምርታ፣ የመምህሩ/ሯ መምሪያ፣ ብሬይል እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን አሟልቷል፣(1%)

I.4. ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት/የንባብ ማዕዘናት፣ የመጫወቻ ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።(2%)

I.5. በትምህርት ቤቱ አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ፣ ሀገር አቀፍየአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ መርሀ ትምህርት፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ መመሪያና ስትራቴጂ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሰነዶች ፣ ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣(1%)

ስታንዳርድ **2**

ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን፣ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረትአሟልቷል (3%) ።

አመልካቾች፡-

2.1. የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን ፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረትለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው፣(1%)

2.2. የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው ።(1%)

2.3. ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶችአሉት።(1%)

ስታንዳርድ **3**

ትምህርት ቤቱ በትምህርት ዘመኑቅድሚያ ሰጥቶ ላቀዳቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል (4%) ፡፡

አመልካቾች፡-

3.1. ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣(1%)

3.2. ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል፣(1%)

3.3. ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ሃብት አሰባስቧል፡፡(1%)

3.4. ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ሰነድ አለው፡፡(1%)

## 2.1.2 ምቹየመማሪያአካባቢ

ስታንዳርድ **4**

ትምህርት ቤቱ ለሕጻናት ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ ሁኔታዎችን ፈጥሯል (10%) ፡፡

አመልካቾች፡-

4.1. አካባቢው የፀዳና ለሕጻናት ተስማሚ የሆነ፣ ንጹህ አየር ያለው፣ ከቆሻሻ መጣያ፣ ከፍሳሽ፣ ከወንዞች፣ ከኩሬዎች፣ ከረግረግና ከገደል የራቀና ሕፃናትን የሚተናኮሉ አውሬዎችና ነፍሳት የሌሉበት ነው፤ (1%)

4.2. ትምህርት ቤቱ በአቅራቢያው ሆስፒታል፤ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ያለው ሆኖ ተላላፊ በሽታ ከሚከላከሉ እንደ ሳንባ ነቀርሳ መከላከያና ከመሳሰሉት የጤና ድርጅቶች የራቀ ነው፡፡ (1%)

4.3. ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣(1%)

4.4. ትምህርት ቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ አለው፣(1%)

4.5. የትምህርት ቤቱ አጥር ግቢ በስታንዳርዱ መሰረት የታጠረ ነው፡፡(1%)

4.6. የትምህርት ቤቱ አካባቢ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት አካቶ ለመንቀሳቀስ፣ ለመጫወትና ለመማር ምቹ ነው፣(1%)

4.7. የትምህርት ቤቱ አካባቢ የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፣ (1%)

4.8. ትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ አካል ጉዳተኛ ላልሆኑ እና ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት የሚመቹ መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር አሟልቷል፡፡(

4.9. 1%)ትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የርዕሰ መምህራን፣ የመምህራን ፣ የረዳት መምህራን ፣የሞግዚቶችና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር አሟልቷል፡፡(1%)

4.10. ትምህርት ቤቱበስታንዳርዱ መሰረትበቂ፣ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው፡፡ (1%)

ስታንዳርድ **5**

ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል (3%) ፡፡

አመልካቾች፡-

5.1. በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ተፈጥሯል።(1%)

5.2. በትምህርት ቤቱ የተቀመጡ ዓላማዎች፣ ግቦችንና ተልዕኮዎችን የተገነዘበና ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምህርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል።(1%)

5.3. በትምህርት ቤቱ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል።(1%)

### **2.1.3** የምድረ ግቢ ገጽታና አደረጃጀት

ስታንዳርድ **6**

ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የመጫወቻ፣ የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎችና ምቹ የመሬት ወለልአሉት።(3%) ።

አመለካቾች

6.1 የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ልዩ ልዩ የመጫወቻና የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎች ያሉት ሆኖ የመሬቱ ወለል ለሕፃናቱ ልዩ ልዩ የአካል እንቅስቃሴ የሚመችና የተስተካከለ ነው። (1%)

6.2. ትምህርት ቤቱ ህፃናት ድብብቆሽ የሚጫወቱበት ቦታ፣ የአሸዋ ሣጥን፣ የአበባና የአትክልት ቦታዎች አሉት። (1%)

6.3. ትምህርት ቤቱ ጥላና ለመዝናኛ የሚያገለግሉ ዛፎች አሉት ፤ (1%)

ስታንዳርድ **7**

ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት (1%) ።

አመልካቾች፡-

7.1. የትምህርት ቤቱ አመራር ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አዘጋጅቷል፤ (1%)

## **II.** ሂደት **45%**

### **2.2.1** እንክብካቤና መማርእና ማስተማር፡-

### **2.2.1.1** እንክብካቤና መማር

ስታንዳርድ **8**

የትምህርት ቤቱ ሕጻናት ተገቢውን እንክብካቤ አግኝተዋል። (5%)

አመልካቾች፡-

8.1. የሕጻናት የግልና የአካባቢ ንፅህና ተጠብቋል።(1%)

8.2. ሕጻናት ተገቢውን የዕረፍትና የመዝናናት እንክብካቤ በማግኘታቸው ምቾታቸው ተጠብቋል፡(1%)

8.3. ሕጻናት ከተላላፊ በሽታና ከድንገተኛ አደጋ የሚጠበቁበት ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል።(1%)

8.4. የሕጻናትን አካላዊ እድገት ለማዳበር እድሜያቸውን መሰረት ያደረገ አካላዊ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ተደርጓል።(1%)

8.5. ትምህርት ቤቱየአመጋገብ መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ተግባራዊ አድርጓል፣(1%)

ስታንዳርድ **9**

የትምህርት ቤቱ ህፃናት ተገቢውን ጥበቃአግኝተዋል (4%) ።

አመልካቾች፡-

9.1. በትምህርት ቤቱ የሕጻናትን አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ስሜታዊ እና ማህበራዊ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። (1%)

9.2. በትምህርት ቤቱ ሕጻናት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ አግኝተዋል።(1%)

9.3. የትምህርት ቤቱ ሕጻናት ራሳቸውን ከተለያዩ አደጋዎች የሚከላከሉበትን ክህሎት አግኝተዋል።(1%)

9.4. ት/ቤቱ በሕጻናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ከተለያዩ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራበት ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል።(1%)

## 2.2.1.2 ማስተማር

ስታንዳርድ **10**

መምህራን የሕጻናቱን የእድገት ፍላጎት፣ፍጥነትና ልዩነት ያገናዘበ የእንክብካቤና የትምህርት እቅድ በማቀድ ተግባራዊ አድርገዋል (4%) ።

አመልካቾች፡-

10.1. የመምህራን የትምህርት እቅድ የሚያስተምሩትን ትምህርትና የሚያደርጉትን እንክብካቤ በተመለከተ ተገቢውን ዓላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ስነ ዘዴወ.ዘ.ተ በአግባቡ አካቷል፣ (1%)

10.2. መምህራን የመጫወቻ እና የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀትና ያሉትንም በመጠቀም ስራ ላይ አውለዋል፣(1%)

10.3. መምህራንየሚያስተምሩት ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ቴሌቭዥን፣ኮምፒውተር፣ ሬዲዮ፣ ቴፕሪከርደር ወ.ዘ.ተ) የተደገፈ ነው።(1%)

10.4. ሕጻናት በራሳቸው ነገሮችን ለመፈተሽ ፣ለመመራመርና ቁሳቁሶችን እንዲገጣጥሙ እና ስዕሎችን እንዲለማመዱ‹ምቹ ሁኔታዎች ተመቻችተውላቸዋል።(0.5%)

10.5. መምህራን የትምህርት ይዘቱን ለህፃናት በሚመጥን ቋንቋ ፣ አቀራረብ እና በታቀደ ጨዋታ መልክ አቅርበዋል።(0.5%)

ስታንዳርድ **11**

መምህራን ሕጻናትን የመንከባከብ እና የትምህርቱን ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ (2%) ።

አመልካቾች፡-

11.1. መምህራን በህፃናት አያያዝ፣ እንክብካቤ እና በሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት በቂ እውቀትና ክህሎት አላቸው፣(1%)

ስታንዳርድ **12**

የት/ቤቱ አመራር፣ መምህራንና ረዳት መምህራን ለሁሉም ህፃናት ተስማሚና ህፃን ተኮር የማስተማር እና የእንክብካቤ ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ህፃናት ንቁተሳትፎ አድጓል (5%) ።

አመልካቾች፡-

12.1. መምህራንና ረዳት መምህራን  ህፃናት ተመራማሪ፣ ችግር ፈቺ እና ራሳቸውን የሚመሩ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፣(1%)

12.2. የትምህርት ቤቱ አመራርህፃን ተኮር የመማርማስተማር ስነ ዘዴና እንክብካቤ  በት/ቤቱ እንዲተገበር ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፣ (1%)

12.3. መምህራንና ረዳት መምህራን  ህፃናትን  እንደ አስፈላጊነቱ በጥንድ፣ በቡድን እና በግል እንዲጫወቱና እንዲማሩ አድርገዋል፣(1%)

12.4. መምህራንና ረዳት መምህራን  ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣(1%)

12.5. መምህራን እና ረዳት መምህራን የእያንዳንዱን/ዷን ህፃን የመማር ፍላጎትና ፍጥነት ያገናዘበ የማስተማር ስነ ዘዴን እና የህፃናት አያያዝን በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ተግባራዊ አድርገዋል።(0.5%)

12.6. መምህራንና ረዳት መምህራን ከህፃናት እንክብካቤ፣ አያያዝና ትምህርት ጋር የተያያዙ  ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ ጥናትናምርምር አካሂደዋል።(0.5%)

### 2.2.2 የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና የህፃናት ግንኙነት

ስታንዳርድ **13**

በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በህፃናት መካከል በመፈቃቀር፣በመከባበርና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ተፈጥሯል(1%) ።

አመልካቾች

13.1. የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና  ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለህፃናት ተገቢውን ፍቅር፣ ክብርና እንክብካቤ በመስጠታቸው ህፃናቱ ደህንነት ተሰምቷቸዋል፤ የመማር ፍላጎታቸውም ጨምሯል።(1%)

ስታንዳርድ **14**

ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትን የተመለከቱ መረጃዎችንይይዛል፣ድጋፍም ይሰጣል (2%) ።

አመልካቾች፡-

14.1. ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎች መዝግቦ ይዟል፤ (1%)

14.2. ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትን የትምህርት አቀባበል ለማሻሻል እና ለማሳደግእንደየፍላጎታቸውና እንደየችሎታቸውልዩ ድጋፍ አድርጓል፣(1%)

ስታንዳርድ **15**

የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን ፣ ሞግዚቶች እና  ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችበልማት ሠራዊት በመደራጀት በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው (2%) ።

አመልካቾች፡-

15.1. የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው የትምህርት ልማት ስራዊት በመገንባት ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መልክ ተወጥተዋል፣ (0.5%)

15.2. መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች በትምህርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፣ (0.5%)

15.3. መምህራን፣ ረዳት መምህራንና ሞግዚቶች እርስ በእርስ በውስጥ ሱፐርቪዥን አማካኝነት ተገነባብተዋል። (0.5%)

15.4. የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን ፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በጥሩ ስነ ምግባር የታነፁ፣ ለሙያቸው ተገቢ ክብር ያላቸው፣ ትምህርት ቤቱን ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑ ናቸው፣(0.5%)

### 2.2.1.4 ስርዓተትምህርት

**ስታንዳርድ 16**

ሥርዓተ ትምህርቱ ተገቢነት ያለው ፣ አሳታፊ እና የህፃናቱን የእድገት ደረጃ፣ ፍላጎቶችና

ልዩነት ያገናዘበ መሆኑን መምህራን እና ረዳት መምህራንገምግመዋል፣ግብረ መልስ ሰጥተዋል።

(3%) ።

አመልካቾች፡-

16.1. መምህራን እና ረዳት መምህራን በሥራ ላይ ያለውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ጠንቅቀው ያውቃሉ፣(1%)

16.2. መምህራን እና ረዳት መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት ከስርዓተ ትምህርቱ ጋር የተጣጣመ ነው፣(1%)

16.3. መምህራን እና ረዳት መምህራንመርሃ-ትምህርቶቹና ሌሎች የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች አሳታፊና ከህፃናቱየዕድገት ደረጃና ፍላጎት ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው ይገመግማሉ፤ ግብረ መልስ ይሰጣሉ። (1%)

## 2.2.1.5 ምዘና

**ስታንዳርድ 17**

ህፃናት በአካል፣በአእምሮ፣ በስሜትና በማህበራዊእድገታቸው የሚያሳዩት መሻሻል በተከታታይ ምዘና ተረጋግጧል (7%) ።

አመልካቾች፡-

17.1. መምህራንና ረዳት መምህራን የህፃናቱን ሁለንተናዊእድገት ዕለት በዕለት በመከታተል የእያንዳንዱን/ዷን ህፃን መረጃ በማህደረ ተግባር/ፖርትፎልዮ/ ይዘዋል።(1%)

17.2. በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና ስርአተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ነው፣(1%)

17.3. በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና ህፃናቱ ዕለት በዕለት በሚያከናውኑት እንቅስቃሴና በሚያሳዩት ባህርይ ላይ የተመሰረተ ነው ፣(1%)

17.4. በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና አንዱን/ዷን ህፃን ከሌላው/ዋ ለማወዳደር ሳይሆን የእያንዳንዱን/ዷን ህፃን የዕድገት ፍላጎትና መሻሻል ላይ ያተኮረ ነው ፣ (1%)

17.5. በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና የልዩ ፍላጎት ህፃናትን አስቀድሞ በማወቅ ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል ነው።(1%)

17.6. መምህራን የህፃናትን የተከታታይ ምዘና በመተንተን ተገቢውን የእንክብካቤና የማስተማር ስልቶችን ተግባራዊ አድርገዋል ፣(1%)

17.7. ትምህርት ቤቱ የህፃናትን ውጤት ለወላጆች በማሳወቅ ግብረ መልስ ተቀብሏል።(1%)

ስታንዳርድ **18**

ትምህርት ቤቱ የሰው ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል (5%) ፡፡

አመልካቾች፡-

18.1. ት/ቤቱ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፣(1%)

18.2. መምህራን እና ረዳት መምህራን በሰለጠኑበት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተመድበው ይሰራሉ፣(1%)

18.3. ርዕሰ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ተመድበው ይሰራሉ፣(1%)

18.4. በት/ቤቱ ያሉ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች እና ተጨማሪ ግብዓቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ውለዋል፣(1%)

18.5. የት/ቤቱ በጀት ቅድሚያ ለተሰጣቸው ተግባራት በተቀመጡና አግባብነት ያላቸው አካላት በወሰኑት መሠረት በተገቢ መንገድ ሥራ ላይ ውሏል።(1%)

## 2.2.1.6 የትምህርትቤት፣የወላጆች/የአሳዳጊዎችናየማህበረሰብአጋርነት

ስታንዳርድ **19**

ትምህርት ቤቱ ከህፃናት ወላጆች/አሳዳጊዎችና ከአካባቢው ማህበረሰብጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው (5%) ፡፡

አመልካቾች፡-

19.1. ትምህርት ቤቱ ወላጆች/አሳዳጊዎች በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤ በትምህርት ቤት ደረጃ ወላጆች/አሳዳጊዎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ በተደራጀ መልኩ እንዲያበረክቱ ያደርጋል።(1%)

19.2. ትምህርት ቤቱ በየወቅቱ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎችና ለአካባቢው ማህበረሰብ በህፃናት የትምህርት አቀባበል፣ የባህርይ መሻሻል፣ የፋይናንስ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃ ይሰጣል፤ ግብረ መልስም ይቀበላል፣(1%)

19.3. ወላጆች/አሳዳጊዎችበወላጅ መምህር ህብረት(ወመህ) እንቅስቃሴ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣(1%)

19.4. ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ በትምህርታቸው እንዲበረታቱ ያግዛሉ፣(1%)

19.5. ወላጆች/አሳዳጊዎች በትምህርት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም መርካታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ፣(1%)

# III. ውጤት 25%

### 2.3.1. የህፃናት ተሳትፎ እና የትምህርት ቤቱ የውስጥ ብቃት

**ስታንዳርድ 20**

**ትምህርት ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት**/Internal Efficiency/ **የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።**(4%)

አመልካቾች፡-

20.1. **ትምህርት ቤቱ በአካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለቅድመ መደበኛ ትምህርት የደረሱ ህፃናት ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ በማድረግ ዕቅዱን አሳክቷል፣**(2%)

20.2. **የትምህርት ቤቱ መጠነ ማቋረጥ በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል፣**(2%)

### 2.3.2 የህፃናትግለ-ስብዕና

ስታንዳድ **21**

ህፃናት በስነ ስርዓት የታነጹ፣ መልካም ስነምግባርን የተላበሱ፣አካባቢን የመንከባከብ ዝንባሌ ያላቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል (10%) ።

አመልካቾች

21.1. ህፃናት በስነ ምግባር የታነፁ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያከብሩ፣እርስ በርስ የሚከባበሩና የሚተጋገዙ ሆነዋል፣(2%)

21.2. ህፃናት የትምህርት ቤቱን ንብረት ለመንከባከብ ያላቸውን ዝንባሌ በተግባር አሳይተዋል፣(2%)

21.3. ህፃናት በደረጃቸው የትምህርት ቤቱን እሴቶች፣ትምህርት ቤቱ ያወጣውን መተዳደሪያ ደንብአውቀው ስራ ላይ በማዋል ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል፣(2%)

21.4. በትምህርት ቤቱ ህፃናት መካከል የመቻቻልና ልዩነትን የመፍታት ዝንባሌ ዳብሯል፣ (2%)

21.5. ህፃናትበደረጃቸውትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል።

### 2.3.3 የመምህራንናየትምህርትአመራርግለ - ስብዕና

ስታንዳርድ **22**

በቅድመ መደበኛትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ተፈጥሯል፣ኪራይ ሰብሳቢነትን የመታገልና የተጠያቂነት ስሜት ዳብሯል (6%) ።

አመልካቾች፡-

22.1. የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ህፃናትን የሚያከብሩና ተግባቢ በመሆናቸው የህፃናት የመማር ፍላጎት ጎልብቷል፣ (2%)

22.2. በትምህርት ቤቱ አመራር ፣ መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣(2%)

22.3. የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል። (2%)

### 2.3.4 የወላጆች/አሳዳጊዎች፣የአካባቢውማህበረሰብእና የአጋር ድርጅቶችተሳትፎ

ስታንዳርድ **23**

የቅድመ መደበኛትምህርት ቤቱ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል።(5%)

አመልካቾች፡-

23.1. ትምህርት ቤቱ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣(2.5%)

23.2. የወላጆች/የአሳዳጊዎች እና የአካባቢው ማህበረሰብተሳትፎ በመጨመሩ ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል።(2.5%)

# 7. የኢንስፔክሽን ሂደት፡-

## 7.1. ቅድመ ኢንስፔክሽን

### 7.1.1. ኢንስፔክሽን የሚካሄድባቸውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን መምረጥ

**የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ከመደረጋቸው በፊት ግልፅ ሆኖ በተቀመጠ መመዘኛ መሰረት መመረጥ አለባቸው። በናሙናነት የሚመረጡ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ትምህርት ቤቶች በፍትሃዊነት ማስተናገድ እንዲቻል፡-**

- አስተዳደራዊ መዋቅር፣
- ሥነ-ምድራዊ አቀማመጥ፣
- ገጠር እና ከተማ እና
- የብቃት ደረጃን ማዕከል በማድረግ መመረጥ አለባቸው።

**ሁሉም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች በሶስት አመት አንድ ጊዜ በኢንስፔክተሮች መታየት ስላለባቸው እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ካሉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመጀመሪያው ዓመት** 20%፣ በሁለተኛው ዓመት 40% እና በሶስተኛው ዓመት 40%ቱን በመውሰድ የኢንስፔክሽን ሥራ እንዲከናወን ይደረጋል። ስብጥሩም የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑትን ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን ያካተተ ሆኖ በናሙናነት የሚመረጡት ከክልል ትምህርት ቢሮ፣ ከዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ/ጽ/ቤት እና ከወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት በጋራ በመሆን ይሆናል።

### 7.1.2. የኢንስፔክሽን ቡድን አመሰራረት፡-

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮ፣ የዞን/የክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ/ጽ/ቤት እና ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት የትምህርት ቤቶችን ኢንስፔክሽን ሲያካሂዱ ቡድኑ የሚዋቀረው በየደረጃው ከሚቋቋመው የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት/የስራ

ሂደት ሆኖ ቢያንስ ሁለት አባላት ሊኖሩት ይገባል። ከተቋቋመው ቡድን አባላት ውስጥ አንዱ የቡድንመሪሆኖ ያገለግላል። በምንም ምክንያት የኢንስፔክሽን ስልጠና ያልወሰደ ባለሙያ ትምህርት ቤት ሄዶ የኢንስፔክሽን ስራ መስራት የለበትም።

### 7.1.3. ከኢንስፔክሽን በፊት ከቅድመ መደበኛ ትምህርትቤቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት፡-

የኢንስፔክሽን ስራ የሚከናወንባቸው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ስለኢንስፔክሽኑ አላማ ከሁለት ሳምንት በፊት እንዲያውቁ መደረግ አለበት። ትምህርት ቤቱም ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ በሚከተለው መልኩ ማዘጋጀት አለበት።

- የትምህርት ቤት ግለ-ግምገማና ደረጃ ምደባ ውጤት
- የትምህርት ቤት ዕቅድ/የአንድ እና የሶስት አመት/
- የህጻናት፣የመምህራን፣የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም የህንጻዎችና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃዎች፣
- የትምህርት ክፍለ ጊዜ ስርጭትና የጊዜ ሰሌዳ፣
- የተደራጀ የህጻናትን ውጤት የሚያሳይ መረጃ፣
- በትምህርት ዙሪያ ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ ት/ቤቱን አስመልክቶ የቀረቡ መሠረታዊ መረጃዎች፣
- የትምህርት ቤቱን የተለያዩ አደረጃጀቶች የሚያሳዩ ሰነዶች።

## 7.2. በኢንስፔክሽን ወቅት

### 7.2.1. የኢንስፔክሽንሥራእንዴትይጀመራል?

የኢንስፔክሽን ቡድኑ ቅድመ መደበኛትምህርት ቤት እንደደረሰ ከትምህርት ቤቱ ር/መምህር/ት እና ሌሎች የትምህርት ቤቱ አመራሮች ጋር በመገናኘት ስለሚከናወነው የኢንስፔክሽን ሥራ ዓላማና አጠቃላይ ሁኔታ ገለፃ ያደርጋል። በመቀጠልም በየደረጃው ለሚደረጉ ውይይቶች ቀጠሮ በመያዝና የትምህርት ቤቱ አመራሮቹን በመጋበዝ ጥያቄ ወይም አስተያየት እንዲያቀርቡና ስለ ትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ሁኔታ ገለፃ እንዲያደርጉ ያደርጋል። ኢንስፔክተሮቹ በኢንስፔክሽን ወቅት በየጊዜው ከትምህርት ቤቱ ር/መምህር/ት ጋር በመገናኘት ከስራው ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥያቄዎችን እና ችግሮችን በአፋጣኝ ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ።

### 7.2.2. ኢንስፔክተሮች እንዴት መረጃይ ሰበስባሉ?

ኢንስፔክተሮች ትምህርት ቤቱን አስመልክቶ ትክክለኛ የአፈጻጸም ውሳኔ ደረጃ ለመስጠት የሚያስችላቸውን መረጃ ለማሰባሰብ ሙሉ ጊዜያቸውን ይጠቀማሉ ። በዚህም መሠረት፡-

- የመማር ማስተማሩን ሁኔታ ይመለከታሉ፣
- የትምህርት ቤቱን ምድረግቢ እና የትምህርት ቤቱን ፋሲሊቲዎች ይመለከታሉ፣
- ከር/መምህሩ/ሯ፣ከመምህራን፣ ከረዳት መምህራን፣ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ውይይት ያደርጋሉ፣
- ትምህርት ቤቱ ከዚህ በፊት ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን ይመለከታሉ፣

ኢንስፔክተሮች በኢንስፔክሽን ወቅት የሰበሰቡትን ማንኛውንም አይነት መረጃ በመረጃ መሰብሰቢያ ቼክሊስት ላይ መመዝገብ አለባቸው። በዚህም መሰረት መረጃው የተደረሰበትን የውሳኔ ሃሳብ እና በውይይት ወቅት የተሰጠ ግብረመልስን ያጠቃልላል።

### 7.2.3. ውሳኔላይመድረስ ፡-

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ውስጥ የተቀመጡትን ስታንዳርዶች ማሟላት አለማሟላቱን በመገምገም ኢንስፔክተሮች ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በውሳኔ አሰጣጡ ሂደትም በማዕቀፉ ውስጥ የተያያዙትን ገላጮችና ቼክሊስቱን መሰረት አድርገውበሰበሰቡት መረጃ አማካይነት ደረጃ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የደረጃ አሰጣጡም፡-

- ደረጃውን ያላሟላ - ደረጃ **1**
- ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ - ደረጃ **2**
- ደረጃውን ያላሟላ - ደረጃ **3**
- ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ - ደረጃ **4** በሚል ይሆናል፡፡

በዚህ መሰረት ኢንስፔክተሮች ለአመልካቾች እና ለስታንዳርዶች ደረጃ በመስጠት ትምህርት ቤቱ በግብዓት፣ በሂደት እና በውጤት ያለበትን ደረጃ በግልጽ ማሳየት በሚያስችል መልኩ ያስቀምጣሉ፡፡ የደረጃ አሰጣጥ ሂደቱም በሚከተለው ምሳሌ መሰረት ይሆናል፡፡

የደረጃ አሰጣጥ ሂደቱ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ውስጥ በተመለከቱት ስታንዳርዶችና አመልካቾች መሰረት ያደረገ ሆኖ፡-

1. በተዘጋጁት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች/ቼክሊስት እና የአመልካች ገላጮችን መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ አመልካች ውጤት መስጠት፤
2. በእያንዳንዱ ስታንዳርድ ውስጥ የሚገኙ አመልካቾች አማካይ ውጤትን በመውሰድ ለስታንዳርዱ ደረጃ መስጠት፤
3. በግብዓት፣ በሂደትና በውጤት ስር ያሉ ስታንዳርዶች አማካይ ውጤት እንደየቅደም ተከተላቸው የግብዓት፣ የሂደት እና የውጤት ደረጃ ይሆናል፤
4. የግብዓት፣ሂደት እና ውጤት ድምር የትምህርት ቤቱ ደረጃ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሠረት የሁሉም መለኪያዎች (ግብዓት ፣ ሂደትና ውጤት) ድምር ውጤት፦

- ከ 50% በታች ከሆነ ትምህርት ቤቱ በደረጃ 1 ይመደባል፡፡
- ከ 50% - 69.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ በደረጃ 2 ይመደባል፡፡
- ከ 70% - 89.99% ከሆነ ትምህርት ቤቱ በደረጃ 3 ይመደባል፡፡
- ከ 90% - 100% ከሆነ ትምህርት ቤቱ በደረጃ 4 ይመደባል፡፡

በመጨረሻም የደረጃ አሰጣጥ ሂደት ዝርዝር አሰራሩ ምሳሌ በዚህ ሰነድ መጨረሻ በተያያዘው ተቀጽላ 3 መሰረት ይሆናል፡፡

## 7.3. ከኢንስፔክሽን በኋላ

### 7.3.1. የቃል ግብረ-መልስመስጠት፡-

ኢንስፔክተሮች በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ቆይታቸው ስላካሄዱት ግምገማ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደርና በክፍል ምልከታ ለታዩ መምህራን ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሚሰጠውም ግብረመልስ ገንቢ፣ የህጻናትን አእምሯዊና አካላዊ ዕድገት ለማምጣት የሚደረገውን ድጋፍ፣ ወደፊት ትምህርት ቤቱ ሊያሻሽል የሚገባውን እና በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኢንስፔክሽኑን ግኝት፣ የተደረሰበትን ውሳኔ፣ እና የተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦችን መሰረት ያደረገ አጠር ያለ

ውይይት መካሄድ አለበት። ከኢንስፔክተሮች የሚሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማስተግበርና ለትምህርት ቤቱ የወደፊት መሻሻል ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ እንዲረዳ በማጠቃለያ ስብሰባው ላይ የጉድኝት ማዕከሉ ሱፐርቫይዘር መገኘት ይኖርበታል።

### 7.3.2. የፅሁፍ ግብረመልስ/ሪፖርት መስጠት፡-

ከኢንስፔክሽን መጠናቀቅ በኋላ የሚሰጠው የፅሁፍ ግብረመልስ በትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬትና በክልል/ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮዎች በጋራ በተዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ መሠረት መሆን ይገባዋል።

ኢንስፔክሽን ያካሄደው አካል ሪፖርቱን ከሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በኢንስፔክሽን የተገኙ ውጤቶችን፣ አስተያየቶችንና የመፍትሔ ሃሳቦችን አጠቃሎ የያዘ አጭር የጽሑፍ ሪፖርት አጠናቅሮ ለትምህርት ቤቱ እና ትምህርት ቤቱ ለሚገኝበት ወረዳ መላክ አለበት። ከዚህ በተጨማሪም እንደ አስፈላጊነቱ ለዞን/ለክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ/ጽህፈት ቤትና ለክልል/ለከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የኢንስፔክሽን ዘርፍ መላክ ይኖርበታል። የየክልሉ/የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮዎች በክልል/ከተማ አስተዳደር የተካሄደ ኢንስፔክሽን አፈጻጸም ሪፖርትን በማጠቃለል ለትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ይልካሉ። የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶቹም ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ አባላት እንዲሁም ለወላጆች/ለአካባቢው ማህበረሰብ ሪፖርቱን በማቅረብ እንዲያውቁትና ለተፈፃሚነቱ ከትምህርት ቤቱ ጎን እንዲሰለፉ ማድረግ ይጠበቅበታል።

### 7.3.3. የቅሬታአቀራረብ

በኢንስፔክሽን ወቅት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቱ በኢንስፔክተሮቹ በአግባቡ አልታየሁም  የሚል ቅሬታ ካደረበት የጽሁፍ ሪፖርት ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በቅርብ ለሚገኘው የኢንስፔክሽን የስራ ክፍል  ቅሬታውን በጽሁፍማቅረብ ይጠበቅበታል። ቅሬታውን የተቀበለው የኢንስፔክሽን የስራ ክፍልም ቅሬታውን መርምሮ ከ 5 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። ቅሬታውን ያቀረበው ክፍል በተሰጠው ምላሽ ካልረካ ቀጥሎ ወዳለው ከፍተኛ የስራ ክፍል ቅሬታውን የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው።በቅሬታ አፈታት ሂደት ቅሬታ የቀረበለት አካል ቅሬታ በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ የማረጋገጥና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎች እንዲያደርጉ በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ ላይተመስርቶ ማከናወን ይጠበቅበታል።

### 7.3.4. ክትትልስለማድረግ፡-

አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሲገመገም ስታንዳርዱን ካሟላና ከስታንዳርዱ በላይ ካገኘ ትምህርት ቤቱ የበለጠ እንዲሻሻል የክትትልና ድጋፍ ስራ በትምህርት ቤቱ ላይ መሰራት አለበት። ትምህርት ቤቱም ያለውን ለውጥ ለማየትና ለማበረታታት እንደገና ከ 3 ዓመት በኋላ እንዲታይ ይደረጋል። ነገር ግን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቱ የተቀመጠውን ስታንዳርድ ያላሟላ ከሆነ ከአንድ አመት በኋላ በድጋሚ በኢንስፔክሽን ይታያል።በዚህም መሰረት ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቱ የሚፈለገውን መሻሻልካላመጣ በየደረጃው የሚመለከታቸው አካላት ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት ይፈጠራል። የጉድኝት ማዕከሉ ሱፐርቫይዘር ትምህርት ቤቱን በቅርብ በመከታተልና በመደገፍ እንዲሻሻሉ የተሰጡ አስተያየቶችን መተግበራቸውን በማረጋገጥ በኩል ከትምህርት ቤቱ ጋር በቅርብ ይሰራል።

የመረጃ ምንጭ

## ተቀጽላ-1 (Appendix)

*የቅድመ መደበኛ ትምህርትቤቶችኢንስፔክሽንማዕቀፍስታንዳርዶች*

## 1.ግብአት (Input) /30%/

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 1.1 የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች (School facility, physical, human and financial resources) | 1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል (5%) ። | 8. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሕንፃዎች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከሲሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ከመሳሰሉት የተሰሩ ናቸው ።<br>9. ህንፃው የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ታሳቢ ባማድረግ የተሰራ ነው ።<br>10. ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ፣ የህፃን-ክፍል ጥምርታ፣የህፃን መምህር ጥምርታ፣ የመምህሩ/ሯ መምሪያ፣ ብሬይል እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን አሟልቷል፣<br>11. ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት/የንባብ ማዕዘናት፣የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የመጫወቻ ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።<br>12. በትምህርት ቤቱ አጠቃላዩ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ፣ ሀገር አቀፍየአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ መርሀ ትምህርት፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ መመሪያና ስትራቴጂ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሰነዶች ፣ ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ | • የት/ቤቱን ህንፃና የመማሪያ ክፍሎቹን በመመልከት፣<br>• የትም/ቤቱን የተለያዩ ፋሲሊቲዎች/ ቁሳቁሶች/ በመቁጠር፣<br>• ርእሰ መምህራንን፣ መምህሩ/ሯንና የሚመለከታቸውን የአስተዳደር ሠራተኞች በማወያየት<br>• ሰነዶችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣ | |
| | 2. ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን፣ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል (3%) ። | • የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን ፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረትለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው፣<br>• የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው ።<br>• ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች አሉት። | • የርዕሰ መምህራን፣ መምህራን ፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች ፕሮፋይል የሚያሳይ መረጃን በመመልከት<br>• የትምህርት ቤቱን አስተዳደር በማወያየት<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| | 3. ትምህርት ቤቱ በትምህርት ዘመኑ ቅድሚያ ሰጥቶ ላቀዳቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል (4%) ። | • ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ሃብት አሰባስቧል።<br>• ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ሰነድ አለው። | • የፋይናንስ ምንጭ እና አጠቃቀም የሚያሳዩ ሰነዶችን በመመልከት<br>• ከትምህርት ቤቱ አመራር ጋር በመወያየት |
| | 4. ትምህርት ቤቱ ለሕጻናት ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ ሁኔታዎችን ፈጥሯል (7%) ። | • አካባቢው የፀዳና ለሕጻናት ተስማሚ የሆነ፣ ንጹህ አየር ያለው፣ ከቆሻሻ መጣያ፣ ከፍሳሽ፣ ከወንዞች፣ ከኩሬዎች፣ ከረግረግና ከገደል የራቀና ሕፃናትን የሚተናኮሉ አውሬዎችና ነፍሳት የሌሉበት ነው፤<br>• ትምህርት ቤቱ በአቅራቢያው ሆስፒታል፤ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ያለው ሆኖ ተላላፊ በሽታ ከሚከላከሉ እንደ ሳንባ ነቀርሳ መከላከያና ከመሳሰሉት | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት፣<br>• ምድረ ግቢውን በመመልከት<br>• የት/ቤቱን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• ሰነዶችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ **(Aspect)** | ስታንዳርድ | አመልካቾች/**Indicators/** | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | የጤና ድርጅቶች የራቀ ነው፡፡<br>• ትምህርት ቤቱ በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣<br>• ትምህርት ቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ አለው፣<br>• የትምህርት ቤቱ አጥር ግቢ በስታንዳርዱ መሰረት የታጠረ ነው፡፡<br>• የትምህርት ቤቱ አካባቢ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት አካቶ ለመንቀሳቀስ፣ ለመጫወትና ለመማር ምቹ ነው፣<br>• የትምህርት ቤቱ አካባቢ የመማር ማስተማር ሂደትን ከሚያውኩ ሁኔታዎች የፀዳ ነው፣<br>• ትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቀ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ አካል ጉዳተኛ ላልሆኑ እና ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት የሚመቹ መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር አሟልቷል፡፡<br>• ትምህርት ቤቱ በቂ፣ ደረጃቸውን የጠበቀ፣ በየጊዜው የሚፀዱና በፆታ የተለዩ የርዕሰ መምህራን፣ የመምህራን ፣ የረዳት መምህራን ፣የሞግዚቶችና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መፀዳጃ ቤቶች ከውሃ እና ሳሙና ጋር አሟልቷል፡፡<br>• ትምህርት ቤቱበስታንዳርዱ መሰረትበቂ፣ ንፁህና የታከመ ለመጠጥ የሚያገለግል የውሃ አቅርቦት አለው፡፡ | |
| | 5. ትምህርት ቤቱ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት ፈጥሯል (3%) ፡፡ | • በትምህርት ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎችን ለመተግበር የሚያስችል አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ተፈጥሯል፡፡<br>• በትምህርት ቤቱ የተቀመጡ ዓላማዎች፣ ግቦችንና ተልዕኮዎችን የተገነዘበና ለመፈፀም ዝግጁ የሆነ የትምህርት ልማት ሰራዊት ተፈጥሯል፡፡ | • ከመምህራንና ከርዕሰ መምህሩ/ሯ ጋር በመወያየት<br>• ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ጋር በመወያየት<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | • በትምህርት ቤቱ ውጤታማ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ሙያዊ ክህሎትና የአመራር ብቃት ተፈጥሯል። | |
| | 6. ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የመጫወቻ፣ የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎችና ምቹ የመሬት ወለል አሉት። (2%) ። | 13. የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ለዩ ለዩ የመጫወቻና የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎች ያሉት ሆኖ የመሬቱ ወለል ለሕፃናት ልዩ ልዩ የአካል እንቅስቃሴ የሚመችና የተስተካከለ ነው። <br> 14. ትምህርት ቤቱ ህፃናት ድብብቆሽ የሚጫወቱበት ቦታ፣ የአሸዋ ጣጥን፣ የአበባና የአትክልት ቦታዎች አሉት። <br> 15. ትምህርት ቤቱ ጥላና ለመዝናኛ የሚያገለግሉ ዛፎች አሉት | • ልዩ ልዩ የመጫወቻና የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎች በመመልከት <br> • የትምህርት ቤቱን ምደረ ግቢ በመመልከት <br> • |
| | 7. ትምህርት ቤቱ የጋራ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች አሉት (1%) ። | • የትምህርት ቤቱ አመራር ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች አዘጋጅቷል፤ | • ከርእሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ጋር በመወያየት <br> • የትምህርት ቤቱን ራዕይ እና ተልዕኮ የሚገልፅ ጽሁፎችን በመመልከት |

# I. ሂደት (Process) /45%/

## 2.1 እንክብካቤና መማርእና ማስተማር፡-

### 2.2.1.1 እንክብካቤና መማር

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| 2.1.1. መማር (Learning) | 8. የትምህርት ቤቱ ሕጻናት ተገቢውን እንክብካቤ አግኝተዋል (5%) ። | • የሕጻናት የግልና የአካባቢ ንፅህና ተጠብቋል። <br> • ሕጻናት ተገቢውን የዕረፍትና የመዝናናትእንክብካቤ በማግኘታቸው ምቾታቸው ተጠብቋል። <br> • ሕጻናት ከተላላፊ በሽታና ከድንገተኛ አደጋ የሚጠበቁበት ስርአት | • የህፃናት የማሸለቢያ ክፍልን በመመልከት <br> • ምድረ ግቢውን በመመልከት <br> • የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ክፍልን በመመልከት <br> • የህጻናት ምግብ ማብሰያና መመገቢያ ክፍሎችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል። <br>• የሕጻናትን አካላዊ እድገት ለማዳበር እድሜያቸውን መሰረት ያደረገ አካላዊ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ተደርጓል። <br>• በትምህርት ቤቱየአመጋገብ መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ተግባራዊ አድርጓል፣ | |
| | 9. የትምህርት ቤቱ ህፃናት ተገቢውን ጥበቃ አግኝተዋል (4%) ። | • በትምህርት ቤቱ የሕጻናትን አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ስሜታዊ እና ማህበራዊ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። <br>• በትምህርት ቤቱ ሕጻናት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ አግኝተዋል። <br>• የትምህርት ቤቱ ሕጻናት ራሳቸውን ከተለያዩ አደጋዎች የሚከላከሉበትን ክህሎት አግኝተዋል። <br>• ት/ቤቱ በሕጻናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ከተለያዩ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራበት ስርአትን ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል። | • ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በመወያየት <br>• ከወመህ ጋር በመወያየት <br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| | 10. መምህራን የሕጻናቱን የእድገት ፍላጎት፣ፍጥነትና ልዩነት ያገናዘበ የእንክብካቤና የትምህርት እቅድ በማቀድ ተግባራዊ አድርገዋል (4%) ። | • የመምህራን የትምህርት እቅድ የሚያስተምሩትን ትምህርትና የሚያደርጉትን እንክብካቤ በተመለከተ ተገቢውን ዓላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ስነ ዘዴወ.ዘ.ተ በአግባቡ አካቷል፣ <br>• መምህራን የመጫወቻ እና የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን በማዘጋጀትና ያሉትንም በመጠቀም ስራ ላይ አውለዋል፣ <br>• መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር፣ ሬዲዮ፣ ቴፕሪከርደር ወ.ዘ.ተ) የተደገፈ ነው። <br>• ሕጻናት በራሳቸው ነገሮችን ለመፈተሽ ፣ለመመራመርና አካባቢያቸውን ለማወቅ ሁኔታዎች ተመቻችተውላቸዋል። | • የመምህራን የትምህርት እቅድን በመመልከት፣ <br>• የትምህርት ማበልፀጊያ ማእከሉን በመመልከት <br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ <br>• መምህራንን እና ር/መምህራንን በማወያየት |

| ንዑስ መስክ **(Aspect)** | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | • መምህራን የትምህርት ይዘቱን ለህፃናት በሚመጥን ቋንቋ ፣ አቀራረብ እና በታቀደ ጨዋታ መልክ ያቀርባሉ፡ | |
| | 11. መምህራን ሕጻናትን የመንከባከብ እና የትምህርቱን ይዘት ጠንቅቀው ያውቃሉ (2%) | • መምህራን በህፃናት አያያዝ፣ እንክብካቤ እና በሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት በቂ እውቀትና ክህሎት አላቸው፣ | • ር/መምህራንን በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ምልከታ በማካሄድ ፣<br>• የመምህራን የትምህርት ዕቅድ በመመልከት |
| | 12. የት/ቤቱ አመራር፣ መምህራንና ረዳት መምህራን ለሁሉም ህፃናት ተስማሚና ህፃን ተኮር የማስተማር እና የእንክብካቤ ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀማቸው የሁሉም ህፃናት ንቁተሳትፎ አድጓል (5%) ። | • መምህራንና ረዳት መምህራን ህፃናት ተመራማሪ፣ ችግር ፈቺ እና ራሳቸውን የሚመሩ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ አሳታፊ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፣<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር ህፃን ተኮር የመማርማስተማር ስነ ዘዴና እንክብካቤ በት/ቤቱ እንዲተገበር ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፣<br>• መምህራንና ረዳት መምህራን ህፃናትን እንደ አስፈላጊነቱ በጥንድ፣ በቡድን እና በግል እንዲጫወቱና እንዲማሩ አድርገዋል፣<br>• መምህራንና ረዳት መምህራን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት ልዩ ድጋፍ ሰጥተዋል፣<br>• መምህራን እና ረዳት መምህራን የእያንዳንዱን/ዷን ህፃን የመማር ፍላጎትና ፍጥነት ያገናዘበ የማስተማር ስነ ዘዴን እና የህፃናት አያያዝን በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ተግባራዊ አድርገዋል።<br>• መምህራንና ረዳት መምህራን ከህፃናት እንክብካቤ፣ አያያዝና ትምህርት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ ጥናትናምርምር አካሂደዋል። | • ር/መምህራንን በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ምልከታ በማካሄድ ፣<br>• የመምህራን የትምህርት ዕቅድ በመመልከት<br>• የህፃናት ማህደረ ተግባርን በመመልከት<br>• የተለያዩ መረጃዎችን በመመልከት<br>• የተሰሩ ተግባራዊ ምርምሮችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 13. በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በህፃናት መካከል በመፈቃቀር፣በመከባበርና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ተፈጥሯል (1%) ። | • የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለህፃናት ተገቢውን ፍቅር፣ ክብርና እንክብካቤ በመስጠታቸው ህፃናቱ ደህንነት ተሰምቷቸዋል፤ የመማር ፍላጎታቸውም ጨምሯል። | • የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብን በማወያየት<br>• ወመህን በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ምልከታ በማካሄድ |
| | 14. ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትን የተመለከቱ መረጃዎችንይይዛል፣ድጋፍም ይሰጣል (2%) ። | • ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎች መዝግቦ ይዟል፤<br>• ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትን የትምህርት አቀባበል ለማሻሻል እና ለማሳደግእንደየፍላጎታቸውና እንደየችሎታቸውልዩ ድጋፍ አድርጓል፣ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ እና ከመምህራን ጋር በመወያየት፣<br>• መረጃዎችን በመመልከት |
| | 15. የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልማት ሠራዊት በመደራጀት በቡድን ስሜት እየሰሩ ነው (2%) ። | • የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው የትምህርት ልማት ሰራዊት በመገንባት ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መልክ ተወጥተዋል፣<br>• መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች በትምርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፣<br>• መምህራን፣ ረዳት መምህራንና ሞግዚቶች እርስ በእርስ በውስጥ ሱፐርቪዥን አማካኝነት ተገነባብተዋል።<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን ፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በጥሩ ስነ ምግባር የታነፁ፣ ለሙያቸው ተገቢ | • ከርዕሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር መወያየት።<br>• ሰነዶችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ **(Aspect)** | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | | ክብር ያላቸው፣ ትምህርት ቤቱን ለማገልገል ቁርጠኛ  የሆኑ ናቸው፣ | |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| **2.2.1.4** **ስርዓተትምህርት** | 16. ሥርዓተ ትምህርቱ ተገቢነት ያለው ፣ አሳታፊ እና የህፃናቱን የእድገት ደረጃ፣ ፍላጎቶችና ልዩነት ያገናዘበ መሆኑን መምህራን እና ረዳት መምህራንይገመግማሉ፣ግብረ መልስ ይሰጣሉ (3%) | • መምህራን እና ረዳት መምህራን በሥራ ላይ ያለውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ጠንቅቀው ያውቃሉ፣<br>• መምህራን እና ረዳት መምህራን የሚያስተምሩት ትምህርት ከስርዓተ ትምህርቱ ጋር የተጣጣመ ነው፣<br>• መምህራን እና ረዳት መምህራንመርሃ-ትምህርቶቹና ሌሎች የስርአተ ትምህርት መሳሪያዎች አሳታፊና ከህፃናቱየዕድገት ደረጃና ፍላጎት ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው ይገመግማሉ፤ ግብረ መልስ ይሰጣሉ። | • የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ምልከታ በማካሄድ፣<br>• ትምህርት እቅዶችን በመመልከት<br>• መምህራን በማወያየት<br>• የስርዓተ ትምህርት ሰነዶች ግምገማን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| **2.2.1.5 ምዘና** | 17. ህፃናት በአካል፣በአእምሮ፣ በስሜትና በማህበራዊእድገታቸው የሚያሳዩት መሻሻል በተከታታይ ምዘና ተረጋግጧል (7%) ፡፡ | • መምህራንና ረዳት መምህራን የህፃናቱን ሁለንተናዊእድገት ዕለት በዕለት በመከታተል የእያንዳንዱን/ዷን ህፃን መረጃ በማህደረ ተግባር/ፖርትፎልዮ/ ይዘዋል፡፡<br>• በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና ስርአተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ነው፣<br>• በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና ህፃናቱ ዕለት በዕለት በሚያከናውኑት እንቅስቃሴና በሚያሳዩት ባህርይ ላይ የተመሰረተ ነው ፣<br>• በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና አንዱን/ዷን ህፃን ከሌላው/ዋ ለማወዳደር ሳይሆን የእያንዳንዱን/ዷን ህፃን የዕድገት ፍላጎትና መሻሻል ላይ ያተኮረ ነው ፣<br>• በትምህርት ቤቱ የሚከናወነው ተከታታይ ምዘና የልዩ ፍላጎት ህፃናትን አስቀድሞ በማወቅ ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል ነው፡፡<br>• መምህራን የህፃናትን የተከታታይ ምዘና በመተንተን ተገቢውን የእንክብካቤና የማስተማር ስልቶችን ተግባራዊ አድርገዋል ፣<br>• ትምህርት ቤቱ የህፃናትን ውጤት ለወላጆች በማሳወቅ ግብረ መልስ ተቀብሏል፡፡ | • የህፃናት ማህደረ ተግባርን በመመልከት<br>• የተከናወኑ ተከታታይ ምዘናዎችን በመመልከት<br>• ልዩ ድጋፍ የተደረገላቸውን ህፃናት መረጃ በመመልከት<br>• ከወላጆች የተገኙ ግበረ መልሶችን በመመልከት<br>• ር/መምህራንንና መምህራንን በማወያየት |
| | 18. ትምህርት ቤቱ የሰው ፣ የገንዘብ እና የንብረት ሃብት አጠቃቀም ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል (5%) ፡፡ | • ት/ቤቱ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አድርጓል፣<br>• መምህራን እና ረዳት መምህራን በሰለጠኑበት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተመድበው ይሰራሉ፣<br>• ርዕሰ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት | • የትምህርት ቤቱን ህንፃ የውስጥ ግብዓቶችን በመመልከት፣<br>• ከርእሰ መምህሩ/ሯ፣ ከመምህራንና ሌሎች ሠራተኞች ጋር በመወያየት፣<br>• ገንዘብ ነክ እና ሌሎች መረጃዎችን በመመልከት |

| ንዑስ መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች | የመረጃ ምንጮች |
| --- | --- | --- | --- |
| | | ተመድበው ይሰራሉ፣<br>• በት/ቤቱ ያሉ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች እና ተጨማሪ ግብዓቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ውለዋል፣<br>• የት/ቤቱ በጀት ቅድሚያ ለተሰጣቸው ተግባራት በተቀመጡና አግባብነት ያላቸው አካላት በወሰኑት መሠረት በተገቢ መንገድ ሥራ ላይ ውሏል። | |
| **2.2.1.6 የትምህርትቤትየወላጆች/ የአሳዳጊዎች ናየማህበረሰብአጋርነት** | 19. ትምህርት ቤቱ ከህፃናት ወላጆች/ አሳዳጊዎችና ከአካባቢው ማህበረሰብጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው (5%) ። | • ትምህርት ቤቱ ወላጆች/አሳዳጊዎች በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤ በትምህርት ቤት ደረጃ ወላጆች/አሳዳጊዎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ በተደራጀ መልኩ እንዲያበረክቱ ያደርጋል።<br>• ትምህርት ቤቱ በየወቅቱ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎችና ለአካባቢው ማህበረሰብ በህፃናት የትምህርት አቀባበል፣ የባህርይ መሻሻል፣ የፋይናንስ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ መረጃ ይሰጣል፤ ግብረ መልስም ይቀበላል፣<br>• ወላጆች/አሳዳጊዎችበወላጅ መምህር ህብረት(ወመህ) እንቅስቃሴ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣<br>• ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ በትምህርታቸው እንዲበረታቱ ያግዛሉ፣<br>• ወላጆች/አሳዳጊዎች በትምህርት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም መርካታቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ። | • ወመህን በማወያየት፣<br>• ከወላጆች ጋር ውይይት የተደረገባቸው ቃለ ጉባዔዎችንበመመልከት፣<br>• የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በማወያየት<br>• ከወላጆች የተሰጡ አስተያየቶችን በመመልከት |

## 3. ውጤት (Outcome) /25%/

| ንዑስ መስክ **(Aspect)** | ስታንዳርድ | አመልካች | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| **2.3.1.** የህፃናት ተሳትፎ እና የትምህርት ቤቱ የውስጥ ብቃት | 20. ትምህርት ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎና የውስጥ ብቃት/Internal Efficiency/ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።(4%) | • ትምህርት ቤቱ በአካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለቅድመ መደበኛ ትምህርት የደረሱ ህፃናት ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ በማድረግ ዕቅዱን አሳክቷል፣<br>• የትምህርት ቤቱ መጠነ ማቋረጥ በዕቅዱ መሰረት ቀንሷል። | • የህፃናት ቅበላ መረጃዎችን በመመልከት<br>• ከወመህ ጋር በመወያየት<br>• የአመቱን የትምህርት ዕቅድና ክንውን በመመልከት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **2.3.2 የህፃናትግለ-ስብዕና** | 21. ህፃናት በስነ ስርዓት የታነጹ፣ መልካም ስነምግባርን የተላበሱ፣አካባቢን የመንከባከብ ዝንባሌያላቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል (10%) ፡፡ | • ህፃናት በስነ ምግባር የታነጹ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያከብሩ፣እርስ በርስ የሚከባበሩና የሚተጋገዙ ሆነዋል፣<br>• ህፃናት የትምህርት ቤቱን ንብረት ለመንከባከብ ያላቸውን ዝንባሌ በተግባር አሳይተዋል፣<br>• ህፃናት በደረጃቸው የትምህርት ቤቱን እሴቶች፣ትምህርት ቤቱ ያወጣውን መተዳደሪያ ደንብአውቀው ስራ ላይ በማዋል ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል፣<br>• በትምህርት ቤቱ ህፃናት መካከል የመቻቻልና ልዩነትን የመፍታት ዝንባሌ ዳብሯል፣<br>• ህፃናት በደረጃቸውትምህርት ቤታቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል፡፡ | • የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• ወመህን በማወያየት<br>• በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ምልከታ በማካሄድ<br>• ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመመልከት፣ |
| **2.3.3 የመምህራንናየትምህርትአመራርግለ - ስብዕና** | 22. በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጥሩ ተግባቦት እና መስተጋብር ተፈጥሯል፣ ኪራይ ሰብሳቢነትን የመታገልና የተጠያቂነት ስሜት ዳብሯል (6%) ፡፡ | • የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ህፃናትን የሚያከብሩና ተግባቢ በመሆናቸው የህፃናት የመማር ፍላጎት ጎልብቷል፣<br>• በትምህርት ቤቱ አመራርመምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነትና በትብብር የመስራት ባህል ዳብሯል፣<br>• የትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራን፣ ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን የሚታገሉና የሚፀየፉ፣ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰሩ ሆነዋል፡፡ | • የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ምልከታ በማካሄድ፣<br>• የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በማወያየት |
| **2.3.4 የወላጆች/አሳዳጊዎች፣የአካባቢውማህበረ** | 23. ትምህርት ቤቱ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት | • ትምህርት ቤቱ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣<br>• የወላጆች/የአሳዳጊዎች እና የአካባቢው ማህበረሰብተሳትፎ በመጨመሩ | • ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በመወያየት<br>• ከወመህ ጋር በመወያየት<br>• ከወላጆች ጋር የተደረጉ ውይቶችን የሚያሳይ ቃለጉባኤ በመመልከት<br>• የተገኘ ድጋፍ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰብእና የአጋር ድርጅቶችተሳትፎ | በመፍጠሩ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ አስገኝቷል። (5%) | ትምህርት ቤቱን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል። | • በልዩ ልዩ መንገድ የተገኙ ድጋፎችን እና የተከናወኑ ትግባራትን/የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳዩ መረጃዎችን በመመልከት |

## ተቀጽላ-2፡ገለጮች /Descriptors/

**ቁልፍ/key/፡-** በውሳኔ አሰጣጥ /ደረጃ ምደባ ሂደት ላይ ውሳኔ ሰጪው አካል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተገንዝቦ ውሳኔ እንዲሰጥ ይጠበቃል።በአጠቃላይ በዚህ ሰነድ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉና በአተረጓጎም ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ታስቦ በመስፈርትነት የተቀመጡ ቃላቶች ከዚህ በታች ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል።

- ከፍተኛ እጥረት/በጣም ዝቅተኛ/አነስተኛ /ውሱን ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር ከ 50 በመቶ በታች ያገኘ፣
- አብዛኛው/አብዛኞቹ/ከፍተኛ ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር 50-69.99 በመቶ ያገኘ፣
- ሙሉ በሙሉ/ሁሉንም ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ 70-89.99 በመቶ ያገኘ፣
- በጣም ከፍተኛ የሚለው ከ 90 ከመቶ እና በላይ ያገኘ፣በሚል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል።

## I. ግብዓት /30%/

| **1.1- የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ፣ ህንፃዎች የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች** | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ስታንዳርድ **1** የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቱ ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያ እና የመገልገያ ህንፃዎች፣ ፋሲሊቲዎች ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች አሟልቷል (5%) ። | | | | |
| አመልካች | ደረጃ **1**<br>ደረጃውን ያላሟላ | ደረጃ **2**<br>ደረጃውን በማሻሻል ላይያለ | ደረጃ **3**<br>ደረጃውን ያሟላ | ደረጃ **4**<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ |
| የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሕንፃዎች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል | በአብዛኛው ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት የተሰሩ የመማሪያና የመገልገያ ህንፃዎች የሉትም። | ትምህርት ቤቱ መማሪያና አገልግሎት መስጫ ህንጻዎችን በስታንዳርዱ መሰረት በአብዛኛው አሟልቷል። | ሁሉምየትምህርት ቤቱ ሕንፃዎች በስታንዳርዱ መሰረትእንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና | ትምህርት ቤቱ የመማሪያ ክፍሎችና ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውሉህንፃዎችከተቀመጠው ስታንዳርድ በላይአሟልቷል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቅርቦት ከሲሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ከመሳሰሉት የተሰሩ ናቸው፡፡ | | | የማቴሪያል አቅርቦት ከሲሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ከመሳሰሉት የተሰሩ ናቸው፡፡ | |
| ህንፃው የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ነው ፡፡ | ህንፃው በአብዛኛው የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ታሳቢ በማድረግ የተሰራ አይደለም ፡፡ | ህንፃው በአብዛኛው የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ነው፡፡ | ህንፃው በስታንዳርዱ መሰረት የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ነው ፡፡ | ህንፃው በስታንዳርዱ መሰረት የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን ታሳቢ በማድረግ የተሰራ ነው ፡፡ በመሆኑም ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት በሚሰጠው አገልግሎት ለሌሎች ት/ቤቶች አርአያ ሆኗል፡፡ |
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ፣ የህፃን-ክፍል ጥምርታ፣የህፃን መምህር ጥምርታ፣ የመምህሩ/ሯ መምሪያ፣ ብሬይል፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን እና የመማሪያ ቁሳቁሶችን አሟልቷል፣ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ፣ የህፃን-ክፍል ጥምርታ፣ የህፃን መምህር ጥምርታ፣ የመምህሩ/ሯ መምሪያ፣ ብሬይል፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን እና የመማሪያ ቁሳቁሶችን በአብዛኛው አላሟላም፡፡ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ፣ የህፃን-ክፍል ጥምርታ፣የህፃን መምህር ጥምርታ፣ የመምህሩ/ሯ መምሪያ፣ ብሬይል፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን እና የመማሪያ ቁሳቁሶችንበአብዛኛው አሟልቷል፡፡ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ፣ የህፃን-ክፍል ጥምርታ፣የህፃን መምህር ጥምርታ፣ የመምህሩ/ሯ መምሪያ፣ ብሬይል፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን እና የመማሪያ ቁሳቁሶችንሙሉ በሙሉአሟልቷል፡፡ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሰረት ፣ የህፃን-ክፍል ጥምርታ፣የህፃን መምህር ጥምርታ፣ የመምህሩ/ሯ መምሪያ፣ ብሬይል፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትን እና የመማሪያ ቁሳቁሶችንበስታንዳርዱ መሰረት ያሟላና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ነው፡፡ |
| ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት/የንባብ ማዕዘናት፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የመጫወቻ ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል፡፡ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት/የንባብ ማዕዘናት፣ ፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የመጫወቻ ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በአብዛኛው አላሟላም፡፡ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት/የንባብ ማዕዘናት፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የመጫወቻ ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በአብዛኛው አሟልቷል፡፡ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት/የንባብ ማዕዘናት፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የመጫወቻ ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል፡፡ | ትምህርት ቤቱ በስታንዳርዱ መሠረት ቤተ-መጽሃፍት/የንባብ ማዕዘናት፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል፣ የመጫወቻ ሜዳ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን ከስታንዳርዱ በላይ አሟልቷል፡፡ |
| በትምህርት ቤቱ አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣ሀገር አቀፍ የአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ መርሀ ትምህርት፣ | በትምህርት ቤቱ አጠቃላይየትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣ሀገር አቀፍየአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ መርሀ ትምህርት፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት  ፖሊሲ | በትምህርት ቤቱ አጠቃላይየትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣ሀገር አቀፍየአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ መርሀ ትምህርት፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት  ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ መመሪያና ስትራቴጂ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተዘጋጁ | በትምህርት ቤቱ አጠቃላይየትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣ሀገር አቀፍየአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ መርሀ ትምህርት፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት  ፖሊሲ | በትምህርት ቤቱ አጠቃላይየትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣ ሀገር አቀፍየአጠቃላይ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ መርሀ ትምህርት፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት  ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ መመሪያና ስትራቴጂ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተዘጋጁ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ መመሪያና ስትራቴጂ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሰነዶች ፣ ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ተሟልተዋል፣ | ማዕቀፍ፣ መመሪያና ስትራቴጂ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሰነዶች ፣ ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው አልተሟሉም፡፡ | ልዩ ልዩ ሰነዶች ፣ ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው ተሟልተዋል፡፡ | ማዕቀፍ፣ መመሪያና ስትራቴጂ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ሰነዶች ፣ ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ በስታንዳርዱ መሰረትተሟልተዋል፣ | ልዩ ልዩ ሰነዶች ፣ ዓለም ዓቀፍ የህፃናት መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎችና የት/ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ በስታንዳርዱ መሰረት የተሟሉና በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴዎች የተደራጁና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ናቸው፡፡ |
| ስታንዳርድ **2** - ትምህርት ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርእሳነ መምህራን፣ መምህራን፣ረዳት መምህራን፣ ሞግዚቶች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል፡፡ | | | | |
| አመልካች | ደረጃ **1**<br>ደረጃውን ያላሟላ | ደረጃ **2**<br>በመሻሻል ላይ ያለ | ደረጃ **3**<br>ደረጃውን ያሟላ | ደረጃ **4**<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ |
| የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን ፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃእና የሙያ ፍቃድ አላቸው፡፡ | በትምህርት ቤቱ ከ 79% በታች ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን ፣ ረዳት መምህራንእና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃእና የሙያ ፍቃድአላቸው ፡፡ | በትምህርት ቤቱ ከ 80-99% ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ እና የሙያ ፍቃድ አላቸው ፡፡ | በትምህርት ቤቱከ 100%ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን፣ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃእና የሙያ ፍቃድ አላቸው፡፡ | በትምህርት ቤቱ ሁሉም ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን ፣ ረዳት መምህራንእና ሞግዚቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃእና የሙያ ፍቃድ አላቸው፡፡ |
| የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው | በትምህርት ቤቱ ከ 50% በታች የሚሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው፡፡ | በትምህርት ቤቱ ከ 50-60% የሚሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው፡፡ | በትምህርት ቤቱ ከ 61-79.9% የሚሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው፡፡ | በትምህርት ቤቱከ 80% በላይድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በስታንዳርዱ መሰረት ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ማስረጃ አላቸው፡፡ |
| ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች አሉት፡፡ | ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች የሉትም፡፡ | አብዛኛዎቹ የት/ቤቱ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ አይደሉም፡፡ | ሁሉም የት/ቤቱ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ ናቸው፡፡ | ት/ቤቱ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን፣ ረዳት መምህራን እና ሞግዚቶች አሉት፡፡ በተጨማሪም ለአካባቢው ማህበረሰብ ሙያዊ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ |
| ስታንዳርድ **3** - ትምህርት ቤቱ በትምህርት ዘመኑ ቅድሚያ ሰጥቶ ላቀዳቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚያገለግል የፋይናንስ ሃብት አሟልቷል (4%) ፡፡ | | | | |
| አመልካች | ደረጃ **1**<br>ደረጃውን ያላሟላ | ደረጃ **2**<br>በመሻሻል ላይ ያለ | ደረጃ **3**<br>ደረጃውን ያሟላ | ደረጃ **4**<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ |
| ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ በዓይነትና | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ | ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቱን በገንዘብ፣ በዓይነትና |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ከአካባቢው ማህበረሰብ (በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት) ሃብት አሰባስቧል፣ | በዓይነትና በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ  የፈጠረው የግንዛቤ ማሳደግ ስራ ባለመኖሩ የተገኘ ድጋፍ የለም። | በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ  የፈጠረው ግንዛቤ ውስን በመሆኑ  የተገኘ ድጋፍ አነስተኛ ነው። | በዓይነትና በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ  የፈጠረው ግንዛቤ ከፍተኛ በመሆኑ  በዕቅዱ መሰረት ሀብት አሰባስቧል። | በጉልበት እንዲደግፍ ትምህርት ቤቱ  የፈጠረው ግንዛቤ ከፍተኛ በመሆኑ  ከዕቅዱ በላይ ሀብት አሰባስቧል። |
| ትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢን በማመንጨት የፋይናንስ አቅሙን አጎልብቷል | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ያሰባሰበው ሀብት አነስተኛ ነው ። | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ለማሰባሰብ ያቀደውን ዕቅድ በአብዛኛው አሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ለማሰባሰብ ያቀደውን ዕቅድ ሙሉ በሙሉ አሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ ከውስጥ ገቢ ለማሰባሰብ ካቀደው በላይ አሳክቷል። |
| ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች  ሃብት አሰባስቧል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ሃብት ለማሰባሰብ ያደረገው እንቅስቃሴ አነስተኛ ነው። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ሃብት ለማሰባሰብ ያቀደውን ዕቅድ በአብዛኛው አሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ሃብት ለማሰባሰብ ያቀደውን ዕቅድ ሙሉ በሙሉአሳክቷል። | ትምህርት ቤቱ በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች  ሃብት ለማሰባሰብ ካቀደው በላይ አሳክቷል። |
| ትምህርት ቤቱ በአግባቡ የተደራጀ የፋይናንስ ሰነድ አለው። | ትምህርት ቤቱ ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት መጠንና አጠቃቀም የሚያመለክት መረጃ የለውም። | ትምህርት ቤቱ ፣ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት ምንጭና መጠን የሚያመለክት መረጃ ያለው ቢሆንም የተደራጀየገቢና ወጪ አመልካች ሰነድ የለውም። | ትምህርት ቤቱ ፣ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት ምንጭና መጠን የሚያመለክት የተደራጀ መረጃ ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ ገቢና ወጪን የሚያመለክት ሰነድ ስለመኖሩ በማስረጃ ተረጋግጧል። | ትምህርት ቤቱ ፣ ከህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ያገኘውን የፋይናንስ ሃብት ምንጭና መጠን የሚያመለክት መረጃ ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ ገቢና ወጪን የሚያመለክት በአግባቡ የተደራጀ ዘመናዊ  የፋይናንስ  የአሰራር ስርአትአለው። |
| ስታንዳርድ **4 -** ትምህርት ቤቱ ለሕጻናት ምቹ፣ የማያሰጋ እና ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥ ሁኔታዎችን ፈጥሯል (7%) ። | | | | |
| አመልካች | ደረጃ **1**<br>ደረጃውን ያላሟላ | ደረጃ **2**<br>በመሻሻል ላይ ያለ | ደረጃ **3**<br>ደረጃውን ያሟላ | ደረጃ **4**<br>ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
